ኢትዮ-ቻምበር በዚህ ሰሞን
Ethio-Chamber Alert
በኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የኮርፖሬት ኮሙኒኬሽንና ህዝብ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት በየ15 ቀኑ የሚዘጋጅ የዜና መጽሄት
ቁጥር 142
ሰኔ 16-30/2009 ዓ.ም.

# ምክር ቤቱ ለሳዑዲ ተፈናቃዮች በሚደረገው የድጋፍ ፕሮግራም ላይ መከረ



*የግሉ ዘርፍ የሳዑዲ ተመላሾችን ለማቋቋም በተጠራው ውይይት ላይ*

የኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ከሳዑዲ አረቢያ ተመላሾችን ለማቋቋም የሚደረገውን ጥረት ለመደገፍ ከግሉ ዘርፍ ተወካዮች ጋር ሰኔ 17 ቀን 2009 ዓ.ም. በሂልተን ሆቴል ዉይይት አካሄደ፡፡

በስብሰባዉ ላይ ከሳዉዲ ዐረቢያ ተፈናቅለዉ ለሚመጡ ወገኖች መንግስት እያደረገ ላለው  መልሶ የማቋቋም ፕሮግራም የግሉ ዘርፍ አገራዊና ማህበራዊ ግዴታውን ከመወጣት አንፃር የበኩሉን አስተዋፅኦ ማበርከት በሚችልበት ጉዳዮች ላይ ውይይት ተደርጓል፡፡ በሳውዲ በህጋዊ መንገድ ሳይመዘገቡ እየኖሩ ያሉ ወገኖች ሳያስቡበትና በድንገት እንዲወጡ በሳውዲ መንግስት ትእዛዝ ስለተሰጣቸው የሚይዙቱም ሆነ  የሚያንጠለጥሉት ንብረት ሳይኖራቸው ወደ ትውልድ ሀገራቸው እየተመለሱ እንደሚገኙ ተገልጿል፡፡

ተሳታፊዎቹ የተለያዩ መንገዶችና አማራጮችን ተጠቅመው በተቻላቸው አቅም ሁሉ ተመላሾቹን እንደሚረዱ በግልፅ ተወያይተዋል፡፡ የገንዘብና የቁሳቁስ እርዳታ በማድረግ፣ የስራ እድል በመፍጠር፣ ስልጠና በመስጠት እና በድርጅታቸው ውስጥ ቀጥሮ በማሰራት ተፈናቃዮቹን በአስቸኳይ ወይም በዘላቂነት መርዳት የሚሉት ከተወያዩባቸው የመርጃ  መንገዶች ውስጥ ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

በመጨረሻም የንግዱን ማህበረሰብ በመወከል ከሚመለከተው አካል ጋር እየተገናኘ የተፈናቃዮችን መልሶ የማቋቋም ስራ የሚያስፈፅም፣ የሚያስተባብርና የሚከታተል አንድ ኮሚቴ ተቋቁሟል፡፡

**በሥራ ፈጣሪነቱ የበቃ ብቻ ሳይሆን**
**በበጎ ምግባሩም የታነፀ የግል ዘርፍ ለመፍጠር እንሥራለን!**

የኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት
የግሉ ዘርፍ ድምፅ

# የኮሪያ ሸቀጥ አስመጭዎች ንግድ ትርኢት በሴዉል ተካሄደ





በኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ምክትል ዋና ፀሀፊ አቶ ውቤ መንግስቱ የተመራው ስምንት አባላት ያሉት የቢዝነስ ልዑካን ቡድን ከሰኔ 15-17 ቀን 2009 ዓ.ም. በሴዉል ከተማ በተካሄደው የኮሪያ ሸቀጥ አስመጭዎች ንግድ ትርኢት ላይ ተሳትፎ አደረገ፡፡ ልዑካን ቡድኑ ከምግብ፣ከመጠጥ፣ከህፃናት መጠቀሚያ ቁሳቁስ፣ከሀይል፣ከኤሌክትሪክ መሳሪያዎች እና ከሌሎች ዘርፎች የተዉጣጡ አባላትን የያዘ ሲሆን ምርቶቻቸውን ከአለም ዙሪያ ለመጡ በርካታ ሀገራት አሳይተዋል፡፡

አቶ ውቤ እንዳሉት የንግድ ትርኢቱ ዓላማ በተለያዩ አገሮች ያሉ ገዢዎች እና ሻጮችን ማገናኘት ሲሆን በዚሁ ዓላማ መሰረት የኢትዮጵያ ቢዝነስ ልዑካን ቡድንም ምርቶቹን ንግድ ትርኢቱ ላይ ለማስተዋወቅ ችሏል፡፡ በተጨማሪም የልዑካን ቡድኑ አባላት በየተሰማሩበት የንግድ ዘርፎች ሌሎች የደረሱበትን የአሰራርና የአፈፃፀም ደረጃ ለመማርና ለማወቅ በማቀድ በንግድ ትርኢቱ ላይ ተሳተፎ እንዳደረጉ ምክትል ዋና ፀሀፊው አክለው ገልፀዋል፡፡

ከዓውደ ርዕዩ ጎን ለጎን ወደ ደቡብ ኮሪያ የሚላኩ ምርቶች ማሟላት ያለባቸው አስፈላጊ ሁኔታዎችና አሰራሮችን አስመልክቶ በተዘጋጀው ወርክሾፕ ላይ የኢትዮጵያ ቢዝነስ ልዑካን ቡድን የነቃ ተሳትፎ አድርጓል፡፡ የኢትዮጵያ የቢዝነስ ልዑካን ቡድን ምርቶቹን በስፋት ያስተዋወቀበትና ሌሎች የቢዝነስ እድሎችንም ያገኘበታል ተብሎ በታሰበው የአቻ ለአቻ የቢዝነስ ስብሰባዎችን /business-to-business (B2Bs) meetings/ ከኮሪያ አቻዎቹ ጋር አካሂዷል፡፡

የቢዝነስ ልዑካን ቡድኑ በኮርያ የኢትዮጵያ አምባሳደር ክቡር ሽፈራው ጃርሶ በመመራት የኮርያ ንግድና ኢንዱስትሪ ምክር ቤትን የጎበኘ ሲሆን የግሎባል ኢኮኖሚ ምርምር ዳይሬክተር ከሆኑት ሚስተር ኦክ ዩን ጋር በቢዝነስ ልማት ድጋፍ፣በአቅም ግንባታ እና የኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር በሚያካሂደው 10ኛው ኢትዮ-ቻምበር አለም ዓቀፍ የንግድ ትርኢት ተሳትፎ ዙሪያ በሚደረጉ ትብብሮች ዙሪያ ውይይት አድርጓል፡፡

በተገኘው መረጃ መሰረት የኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት፣የኮርያ ንግድና ኢንዱስትሪ ምክር ቤት እና ኢምባሲው ወደፊት በሚካሄደው የኢትዮጵያ ምርቶችን የማስተዋወቅ ሴሚናር/ Ethiopian product promotional Seminar/ በተመለከተ እንደሚወያዩና የጋራ የድርጊት መርሀ-ግብር እንደሚያዘጋጁ ይጠበቃል፡፡

“የንግድና ኢንቨስትመንት ኢንፎርሜሽን ሊያገኙ የሚችሉበትን የመረጃ ማዕከል በምክር ቤቱ 7ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 114 በመሄድ እንዲጎበኙ በአክብሮት ተጋብዘዋል”

አገልግሎት የሚሰጥበት ሰዓት -ከሰኞ-አርብ ፤ከ3-11 ሰዓት

ዋና አዘጋጅ፡- ደበበ አበበ
አዘጋጆች፡- ዮሴፍ ተሾመ
ጥበቡ ታዬ
ካሜራ፡- ያሬድ አባቡ
ፕሮቶኮል፡- ሲሳይ አስታጥቄ

አድራሻ፡-
ስልክ፡- +251-115-54-09-93
ፋክስ፡-+251-011-5517699
ኢሜል፡- ethchamb@ethionet.et
ድረ-ገጽ፡- www.ethiopianchamber.com

Ethio-Chamber Alert

Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations,
Corporate Communication and Public Relations Directorate Bi-monthly News Letter

No. 142 June 23– July 7, 2017

# ECCSA Holds Meeting on Rehabilitation of Saudi Repatriates



Private Sector Discussing on the Issue of Rehabilitation of Saudi Repatriates

The Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations (ECCSA) organized a meeting on June 24, 2017 at Hilton Hotel and discussed with the representatives of the local business companies on how to rehabilitate the returnees from Saudi Arabia.

The meeting entertained various issues on how the private sector should work together and contribute its part for supporting the efforts being exerted to rehabilitate the returnees.

It was stated that some of the returnees who need to be rehabilitated are coming back to their homeland, Ethiopia, without any money and property, since the situation was unexpected and urgent for them.

The participants discussed on the issue openly and stood firmly to support the returnees as much as they could. Accordingly, different options on how to support the returnees urgently and sustainably were proposed. Donating financial and material supports, providing trainings, creating job opportunities for the returnees and hiring them are some of the kinds of supports proposed by the participants. The Pledge forms to be filled in were distributed to the representatives of the private companies.

After discussing on various issues and options concerning on how to support the returnees, the participants formed a committee, which, representing the private sector, is going to undertake, coordinate and follow up activities related to the rehabilitation of the returnees.

It is noted that ECCSA organized this kind of discussion for the second time on similar issues.

We strive for the creation of entrepreneurial and ethical businesses!
Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations
Voice of the Private Sector

# Korean Importer Goods Fair 2017 Held in Seoul, Korea

- **8 members Ethiopian business delegation Participates**

8 members of Ethiopian business delegation headed by Ato Woubie Mengistu, Deputy Secretary General of the Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations, participated on the Korean Importer Goods Fair 2017 held from June 22-24/2017, at COEX, Seoul, Korea. The delegation comprised of Food, Beverage, Children's Items, Energy Items, Electronic Appliances and other sectors exhibited products to buyers from various countries.

According to Ato Woubie, the aim of the fair was to create linkages between buyers and sellers of different countries, and the Ethiopian business delegation paid the visit with a purpose of getting and dealing with buyers to the local products. The delegation also aimed at learning from others status of practices and level of performances in the area of their business choices, the Deputy Secretary said.

In line with the product exhibition, the Ethiopian businesses showed active participation on a workshop organized on the requirements and procedures of export products to South Korea. It was also stated that there was an extensive business-to-business (B2Bs) meetings between the Ethiopian businesses and their counterparts from the Republic of Korea, which was supposed to be valuable both in accessing buyers and opening eyes for other opportunities.

In the meantime, headed by His Excellency Shifraw Jarso, Ambassador of the Embassy of Ethiopia to Korea, the delegation paid a visit to the Korean Chamber of Commerce and Industry and made discussion with Mr. Ok Yun, Director of the Global Economic Research Team on areas of cooperation such as business development support, capacity building and participation in the 10th Ethio-Chamber International Trade Fair which will be organized in the coming October. The first task of the cooperation, as proposed, is said to revolve around the organization of a seminar that aims at promoting Ethiopia as a country and its products in the land of Korea on a tentative schedule to be held in Seoul on the coming November.





According to available information, KCCI, ECCSA & the Embassy shall discuss on the proposed Ethiopian product promotional Seminar by KCCI and develop joint action plan.

"You are kindly invited to use the Resource and WTO Reference Center at ECCSA Building 7th floor room number 714. You will get trade and investment information."

Service Hours-Monday-Friday, from 9.00 am-5.00 pm

**Editor-in-Chief:** Debebe Abebe
**Editors:** Yosef Teshome
Tibebu Taye
**Photographing:** Yared Ababu
**Protocol:** Sisay Astatke

**Address:**
**Tell:** +251-115-54-09-93
**Fax:** +251-011-5517699
**Email:** ethchamb@ethionet.et
**Website:** www.ethiopianchamber.com